**ዮም ፍሥሓ ኮነ!**
**በእንተ ርደተ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ኵላ ምድር፡**
**ዘኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር!**

**ዛሬና እንግዴህ ወዲህ፡ ደስታ ኾነ!**
**መንፈስ ቅዱስ፡**
**ሙላዋ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ በኾነችው፡**
**በምድር ኹሉ ላይ፡ በምልዓት ወርዷልና!**

\+ + +

# ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች የተላለፈ ማሳሰቢያ።

## በባዕዳን ዘንድ፡ "የአባቶች ቀን" እና "የእናቶች ቀን" እየተባሉ ስለሚከበሩት በዓላት።

---

*ባዕዳን፥ በተለይም፡ ምዕራባውያን ሕዝቦች፡ እምነታቸውና ሥጋዊ ሥልጣኔያቸው፥ የዘመኑ ዓለማዊ ኑሮአቸውም ብክነት ባስከተለባቸው ግዴታ መነሻነት ሊኾን ይችላል፡ የያገራቸው ባህል ኾኖ፡ "የአባቶች ቀን" እና "የእናቶች ቀን" እያሉ፡ በተለያየ ዕለት፡ በዓመት በዓልነት የሚያከብሩዋቸው፡ ኹለት ቀኖች መኖራቸው ይታወቃል።*

*በዓለሙ ኹሉ የተበተናችሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት፡ ማኅበራዊው ኑሮአችሁ እያስገደዳችሁ፡ ኹለቱንም በዓላት፡ ማለትም፡ "የአባቶች ቀን" እና "የእናቶች ቀን"፡ የሚባሉትን ዕለታት፡ እንደያገሩ ባህል፡ በያላችሁበት ማክበራችሁ እንደማይቀር ይታመናል።*

ይኹን እንጂ፡ እኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያውያት፡ የማንንም ሰብአዊ ፍጡር ባህል የማንነቅፍ ብንኾንም፡ በዚህ ረገድ፡ ከእግዚአብሔር፡ በቅዱሱ ኪዳን አግኝተን የኖርንበት፥ አኹንም እየኖርንበት ያለነው፥ ወደፊትም የምንኖርበት፥ ልንከተለው የሚገባንም፡ የራሳችን የኾነ፡ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ስላለን፡ ይህንኑ አውቃችሁት፡ በተግባር ላይ ማዋላችሁን ትቀጥሉበት ዘንድ እያሳሰብናችሁ፡ በኪዳናዊ ኢትዮጵያዊነታችሁ ተመልክታችኋቸው፡ ተገቢውን ለመፈጸም ትችሉ ዘንድ፡ ይህን የመሰለውን ሕያው ቅርሳችንን የሚያጸኑ፡ ኢትዮጵያውያት ቊምነገሮችን፡ በአጫጭር በማውሳት፡ ከዚህ እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል፡-

፩ኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ በሥጋ ወላጆችና ተወላጆች መካከል ያለው የፍቅር ግንኙነት፡ ገና፡ ከልደት ጀምሮ፡ በዓመቱ ሰዓታትና ዕለታት፥ ሳምንታትና ወራትም ብቻ ሳይኾን፡ በሕይወተ ሥጋ እስካሉ ድረስ፡ ያለማቋረጥ፡ ለዘወትር፡ ሲታወስና ሲከበር የሚኖር እንጂ፡ በዓመት፡ ለአንድ ቀን ብቻ ተወስኖና ታስቦ የሚከበር አለመኾኑ፡ በይፋ የሚታወቅ ነው።

ስለዚህ፡ በሰብአዊነት ደረጃ እንኳ፡ ለሥጋ ወላጆችና ተወላጆች የምናደርገው፡ ይህ፡ ያማረው መልካሙ ባህላችን፡ በምንም ዓይነት መመዘኛና መሥፈሪያም ቢኾን፡ ከባዕዳኑ ጋር ሊነጻጸር፥ ወይም፡ ሊወዳደር ስለማይችል፥ ሊያስቡትም ስለማይገባ፡ በዚህ ረገድ፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ በባዕዳኑ ባህል ተተክቶ፥ ወይም፡ ተመሣጥሮም ቢኾን፡ እንዲከበር ለማድረግ፡ በገሃድም ኾነ፡ በረቂቅ የተንኰል መንገድ፡ የሚደረገውን ሙከራ፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የማንቀበለው፥ እንዲያውም፡ የምንቃወመው መኾኑ፡ ከወዲሁ ሊታወቅ ያስፈልጋል።

የዚህም ምክንያት፡ ይህ ነገር፡ በእኛ በኪዳናውያን ኢትዮጵያውያንና በኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ ከዚህ፡ ከሥጋዊ ባህልነቱ ገጽታ ይልቅ፡ እጅግ የሚበልጥ፡ ሌላ ዓቢይ ሃይማኖታዊ መሠረት ያለው በመኾኑ ነውና፡ ይኸው እውነታ፡ ከዚህ በታች፡ በተከታታይ፡ በሠፈሩት፡ ውሱን ሓተታዎች ስለተገለጸ፡ እነዚህኑ ሓተታዎች፡ በጥሞናና በማስተዋል መመልከቱ፡ ለማነኛችንም ጠቃሚ ይኾናል።

፪ኛ: የቃል ኪዳን አምላካችን እግዚአብሔር፡ በእግዚአብሔር አብነቱ፡ በሥጋ፡ ስለፈጠረን፥ በነፍስና በመንፈስም፡ ስለወለደን፡ "አባት!" ወይም: "አባታችን!" ብለን የምንጠራውና በዚህ ማንነቱ: በዓመቱ ውስጥ: በስሙ እንድናከብራቸው: በዓላትን የመደብንለት: የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ አባት፥ የእኛም አባታችን የኾነው: አንዱ ልዑል እግዚአብሔር አብ ብቻ ነው::

፫ኛ: ራሱ፡ እግዚአብሔር በሠራውና የእርሱ በኾነው፡ በተቀደሰው መለኮታዊ ሥርዓተ ጋብቻ መሠረት፡ የእግዚአብሔር ሙሽሪት እንደመኾኗ፡ በእግዚአብሔር እምነቷ (እናትነቷ)፡ በሥጋ፡ ስለፈጠረችን፥ በነፍስና በመንፈስም፡ ስለወለደችን፡ "እናት" ወይም: "እናታችን!" ብለን የምንጠራትና በዚህ ማንነቷ: በዓመቱ ውስጥ: በስሟ እንድናከብራቸው በዓላትን የመደብንላት: መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፥ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ እናት፥ የእኛም እናታችን የኾነችው፡ አንዲቷ እግዚአብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ ናት::

፬ኛ: እኛ: የሥጋ ወላጆችና ተወላጆች: እንዲህ፡ ከእግዚአብሔር አብ እና ከእግዚአብሔር እም፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ በሥጋ ተፈጥረን፥ በነፍስ እና በመንፈስም፡ ከእነርሱ የተወለድን በመኾናችን: ኹላችንም: የእርሱ: የእግዚአብሔር አብ፡ የአንዱ አባታችን እና የእርሷ: የእግዚአብሔር እም፡ የአንዲቷ እናታችን ልጆች ነን::

፭ኛ: እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለእኛ: የዘለዓለማዊ ሕይወትን ዘውድ ሊያቀዳጀን: በእግዚአብሔር አብ አባትነት እና በእግዚአብሔር እም እናትነት፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከሰብአዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም: በሰውነት ተወልዶ፡ ራሱን ብቻ ሳይኾን፡ የሥጋ ወላጆችና ተወላጆች የኾንነውን: እኛን ጭምር: የአባቱ፡ የእግዚአብሔር አብ እና የእናቱ፡ የእግዚአብሔር እም ልጆች አደረገን።

፮ኛ: በአሮጌው ኪዳን: **"አክብር አባከ፥ ወእመከ!"** ማለትም: "አባትህንና እናትህን አክብር!" የሚለው መለኮታዊ መመሪያ: ለሥጋ ተወላጆች የተሰጠው ለምን እንደኾነ: በትክክል መረዳት ያስፈልገናል።

ይኸውም፡ የሥጋ ወላጆች፡ የእውነተኞቹና የዘላለማውያኑ አባትና እናት፡ የልዑል እግዚአብሔርና የድንግል ማርያም፡ ባለአደራዎችና ተጠሪዎች በመኾን፡ በሥጋ የወለዷቸውን ተወላጆች፡ በጥንቃቄና በእንክብካቤ እንዲያሳድጓቸው፥ የሥጋ ወላጆችም፡ የእግዚአብሔርን እምነትና ምግባር፥ ሥርዓትና ሕይወት ጠብቀው እስከኖሩ ድረስ፡ የሥጋ ተወላጆች እንዲያከብሩዋቸው መኾኑን በማመን፡ የሥጋ ወላጆችም ኾኑ፡ ተወላጆች፡ ይህን፡ የየቅል ኃላፊነታቸውን አውቀውት፡ ግዴታቸውን፡ በየፊናቸው እንዲወጡ ሊያሳስብ ነው:: (ዘፀ. ፳፥ ፲፪። ማቴ. ፲፭፥ ፬-፱::)

ይህም መመሪያ የሚጸናው፡ በአዲሱ ኪዳን፡ "ዘያፈቅር አባሁ፥ ወእሞ እምኔየ፡ ኢይደሉ ሊተ፤ ወኢይክል ይጸመደኒ። ወዘያፈቅር ወልዶ፥ ወወለቶ እምኔየ፡ ኢይደሉ ሊተ፤ ወኢይክል ይጸመደኒ።"

ማለትም፡ "ከእኔ ይልቅ፡ አባቱንና እናቱን የሚወድድ፡ ለእኔ ሊኾን አይገባውም፤ ዐብሮኝ ሊኾንም አይችልም። እንዲሁም፡ ከእኔ ይልቅ፡ ወንድ ልጁንና ሴት ልጁን የሚወድድ፡ ለእኔ ሊኾን አይገባውም፤ ዐብሮኝ ሊኾንም አይችልም።" የሚለው መለኮታዊ ቃል፡ እንደተጠበቀ መኾኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

፪ኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን መሠረት፡ "ወኢትሰምዩ አበ፡ በዲበ ምድር! እስመ አሓዱ ውእቱ፡ አቡክሙ ሰማያዊ።" ማለትም፡ “አባታችሁ አንዱ፥ እርሱም፡ የሰማዩ ብቻ ነውና፡ በምድር ላይ፡ ማንንም፡ “አባት!” ብላችሁ አትጥሩ!”

ደግሞም፡ "ወአንትሙሰ፡ አኀው ኵልክሙ!" ማለትም፡ "እናንተ ግን፡ ኹላችሁም፡ ወንድማማች ናችሁ!" የሚለው መለኮታዊ ቃል፡

"ወኢትሰምዩ እመ፡ በዲበ ምድር! እስመ አሓቲ ይእቲ እምክሙ ሰማያዊት።" ማለትም፡ “እናታችሁ አንዲት፥ እርሷም፡ የሰማይዋ ብቻ ናትና፤ በምድር ላይ፡ ማንንም፡ "እናት!" ብላችሁ አትጥሩ!”

ደግሞም፡ "ወአንትሙሰ፡ አኃት ኵልክሙ!" ማለትም፡ "እናንተ ግን፡ ኹላችሁም፡ እኅትማማች ናችሁ!" የሚለውን ስለሚያካትት፥ ይህ መለኮታዊ መመሪያ፡ መጠበቅና መከበር፥ መፈጸምም እንዳለበት፡ ምንጊዜም፡ ሊታሰብ ይገባል:: (ማቴ. ፳፫፥ ፱::)

\+ \+ \+